# ለተወደዳችሁ የጎዋ ሰሌዳችን ተከታታዮች!

ከጥቂት ወራት በፊት፡ የአገልግሎታችንን ተግባር ለመፈጸም፡ ወደኢትዮጵያ ተጉዘን ነበረ፡፡ በዚያ ጉዟችን፡ ወደአንዳንድ የኢትዮጵያ ከተሞች ብቻ ሳይኾን፡ እጅግ ተራራማና ሩቅ፥ የእግርና የከብት መንገዳቸውም፡ በጣም አደገኛ ወደኾኑ የገጠር ሥፍራዎችም ዘልቀናል፤ እነዚያ ሥፍራዎች፡ የእለቄጥሩ (electric) ኃይልንና ረቂቅ መገናኛን የመሰሉት፡ የዘመኑ የሥልጣኔ ውጤቶች ገና ያልደረሱባቸው በመኾናቸው፡ የጎዋ አውታር (internet) መልእክት ለማስተላለፍ አልተቻለንም፡፡

ይህ ጉዟችን፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነትን፡ ከሃይማኖቱና ከሥርዓቱ ጋር፡ ከጥንት ጀምረው እስከዛሬ ድረስ እንዴት ሊያቆዩን እንደቻሉ፥ ማለትም፡ ይህን ሕያውና ዘለዓለማዊ ቅርስ ለማቆየት፡ ምን ዓይነት መሥዋዕትነትን እንደከፈሉ፡ በቀላሉ አስረድቶናል፡፡

ቀደም ብለው፡ በጎዋ ሰሌዳችን (web site) ላይ የወጡት መልእክቶች፡ እምብዛም ሳይለወጡ የቆዩት፥ ከእናንተም፡ ለደረሱን ጥያቄዎቻችሁና አስተያየቶቻችሁ መልስ ሳንሰጥ የዘገየነው፡ በዚህ ምክንያት መኾኑን አውቃችሁት፡ ይቅርታ እንድታደርጉልን እንጠይቃለን፡፡

ከዚያ ከባድ ጉዟችን ከተመለስን በኋላ፡ ለእነዚያ ወገኖቻችን የጻፍነው ደብዳቤ፡ በጉብኝታችን ጊዜ የኾነውንና የተመለከትነውን፥ ከእርሱም የተገኘውን ውጤት፡ በመጠኑም ቢኾን የሚያስረዳ ስለኾነ፡ እናንተም፡ አንዳንድ ትምህርታውያን የኾኑ ቊም ነገሮችን እንደምትቀስሙበት በማመን፡ ፍሬ ነገሮቹን አውጣጥተን፡ እንደሚከተለው አቅርበንላችኋል፡፡

# ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት፡፡

# Ethiopia: The Kingdom of God Services

ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መኾኗን፥ ኢትዮጵያውያንም፡ የቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ መኾናቸውን ለማስረዳት፥ የ“ኢትዮጵያ” እና “የኢትዮጵያውያን” የኾነውንም ኹሉ ለመጠበቅና ለማሳወቅ፡፡
To reveal the truth about Ethiopia's entity as the Kingdom of God and Ethiopians' identity as the People of the Holy Covenant with God; and so, to safeguard and promote all that pertains to Ethiopia and Ethiopians.

ታኅሣሥ ፲፯ ቀን፥ ፲፱፻፺፱ ዓ.ም.

**በስመ እግዚአብሔር አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ፥ አሐዱ አምላክ፤**

**በስመ እግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ፥**
**አንበሳ መዋኢ፡ ዘእምነገደ ይሁዳ፥ ሥርዉ ለዳዊት፥**
**ካህኑ ለዓለም፡ በከመ ሢመቱ ለመልከ ጼዴቅ ኢትዮጵያዊ፥**
**ንጉሠ ጽዮን ወንጉሠ ነገሥት ወንግሥታት ዘኢትዮጵያ፤**

**በስመ እግዝእትነ ወእምነ ወመቅደስነ ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ፥**
**እንተ ይእቲ ሀገሪትነ ኢትዮጵያ፡**
**ዘታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር፡ በእንተ ኵሉ ዓለም፥**
**ንግሥተ ጽዮን ወንግሥተ ነገሥት ወንግሥታት ዘኢትዮጵያ፤**

---

ይድረስ፡-
በ....... ክፍለ ሀገር፥ በ....... አውራጃ፥ በ....... ወረዳ፥
በቀበሌ @3 ውስጥ ተጠቃልላችሁ ለምትኖሩ፡
ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን፡ የ፯ቱ ሰበካ ጉባኤዎች አባሎች ካህናትና ምእመናን፤
መካነ ሓዋርያት፤ ኢትዮጵያ፡፡

ስመ ጥሩው ኢትዮጵያዊ ሓዋርያ፡ .......፡ ወስመ ጥምቀቱ፡ .......፡ መሥርተዋትና ሓዋርያዊ ተልእኳቸውን ሲያካኼዱባት የኖረችውን፡ የ....... ቤተ ክርስቲያንን በዓል ለማክበር፡ ባለፈው ጥቅምት 5 ቀን፥ 09)(9 ዓ.ም. ወደዚችው ቀበሌያችሁ መጥተን፡ ዓይተናችሁና ተዋውቀናችሁ ከተመለስንበት ጊዜ ጀምሮ፡ “እንደምን ባጅታችኋል?” እያልን፡ የአክብሮት ሰላምታችንን እናቀርብላችኋለን፡፡

ቸርና ኃያል ለኾነው፡ ለዓለሙ መድኃኒት፡ ለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፥ ለቅድስት እናቱም፡ ለድንግል ማርያም፡ ምስጋናችን ይድረሳቸውና፡ እኛ፡ በእነርሱ ረድኤት ተጠብቀን፡ ከመኖሪያችሁ ደርሰን ለመመለስ የበቃንበትን፡ ረዥሙንና ከባዱን ጒዟችንን፡ በሰላም ፈጽመንና አዲስ አበባ ደርሰን፡ በደህና ኹኔታ ላይ እንገኛለን፡፡

እስካኹን መልስ ሳንሰጣችሁ የቆየነው፡ አዲስ አበባ እንደገባን፡ አንዳንድ ያልታሰቡና አስቸኳዮች የኾኑ የአገልግሎታችን ሥራዎች ጠብቀውን ስላገኙን፡ “እነርሱን በቅድሚያ እንፈጽም፥ ይህንም፡ ለእናንተ ልንልክ ያሰብነውን በረከት እናዘጋጅ!” ብለን በመኾኑ ነውና፡ ይህንኑ አውቃችሁት፡ ይቅርታ እንድታደርጉልን እንጠይቃችኋለን፡፡

---

መልእ. ሣ. ቁ. 8)02፤ ስልክ ቁ. 06-08-*5፤ "--*5፤ አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ፡፡
P. O. Box 812, Tel. Nos. 16-18-85; 20-00-85, Addis Abeba, Ethiopia.
P.O.Box 43262, Washington, DC 20010-9262 U.S.A.
Tel. (301) 587-8074 ~ Fax: 301-587-1971 ~ E-mail: ekogyesus@aol.com
**Website: www.ethkogserv.org**

ክቡራንና ክቡራት፡-

ከኹሉ አስቀድሞ፡ እኛ፡ ልናሳውቃችሁ፥ እናንተም፡ ልታውቋቸው የሚገቡ ቍም ነገሮች ስላሉ፡ እነዚህን ቍም ነገሮች፡ ከዚህ እንደሚከተለው ዘርዝረን አቅርበንላችኋል፡-

1ኛ፡ እያንዳንዱ ሰው፡ በእግዚአብሔር መልክ በተፈጠረበት ሰውነቱ፡ በተለይም፡ የመልከ ጼዴቅን የቃል ኪዳን ጸጋና በረከት የተቀዳጀው፡ ኢትዮጵያዊው ወገናችን፡ ያለምንም ርዳታና ድጋፍ፡ በራሱ የተፈጥሮ፥ ወይም፡ የትምህርት ሙያ ብቻ፡ ሠርቶ፥ ሰብአዊ ክብሩን ጠብቆና ራሱንም ችሎ የመኖር ዓቅምና ብቃት አለው፤ የእኛ የአገልግሎት ዓላማ፡ ይህን እውነታ ለእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በማሳወቅ፡ ያን ኢትዮጵያዊ፡ በነፍሱና በሥጋው፥ በመንፈሱም፡ ከባዕዳን ተረጅነትና ተመጽዋችነት፥ በጠቅላላም ከልመና ቀንበር ነጻ ማውጣትና ለዚያ፡ ከላይ ለተጠቀሰው፡ ለእውነተኛው የኢትዮጵያዊነት ሕይወት እንዲበቃ ማድረግ ነው።

ስለዚህ፡ በእኛ በኩል፡ ለእናንተ የምናበረክተው ማናቸውም ዓይነት የተልእኮ ግዳጅ፡ "አገልግሎት" እንጂ፡ እንደእርዳታ፥ ወይም፡ እንደምጽዋት ተቆጥሮ፡ እየራሳችሁን፡ እንደተረጂና እንደተመጽዋች የሚያስቆጥር እንዳይመስል፡ ኹላችንም ልንጠነቀቅበት ያስፈልጋል። አገልግሎታችን፡ እንዲህ የሚለውን፡ የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ቃል የተከተለ መኾኑን፡ ልትገንዘቡት ይገባል፡-

"ዘይፈቅድ እምኔክሙ፡ ይኩን ዐቢየ፥ ይኩንክሙ ላእከ! ወዘሂ ይፈቅድ እምኔክሙ፡ ይኩን ሊቀ፥ ይኩንክሙ ገብረ! እስመ ኢመጽአ ወልደ እጓለ እመሕያው ከመ ይትለአክዎ፥ ዘእንበለ ዳእሙ ከመ ይትለአክ፥ ወየሀብ ነፍሶ ቤዛ ብዙኃን።"

"ማንም፡ ከእናንተ፡ ታላቅ ሊኾን የሚወድ፡ የእናንተ አገልጋይ ይኹን! ከእናንተም፡ ማንም አለቃ ሊኾን የሚወድ፡ የእናንተ ባሪያ ይኹን! የእግዚአብሔር አብ ልጅና የድንግል ማርያም ልጅ የኾንሁት፡ እኔ፡ ጌታችሁና መምህራችሁ እንኳ፡ ላገለግል፥ ራሴንም፡ ለብዙዎች ቤዛ አድርጌ ልሰጥ እንጂ፡ ሊያገለግሉኝ አልመጣሁምና።"

(ማቴ. "፥ "6-"8።)

2ኛ፡ የአገልግሎት አቋማችን፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታችንን በመከተል፡ ይህን አገልግሎት የሚያበረክተው፡ አባሎቹ፡ እያንዳንዳቸው፡ በየግላቸው በሚያስገኙት ገቢ ብቻ እንጂ፡ ከሌላ፡ ከውጭ የሚጨመር፡ አንዳችም ነገር ኖሮ አይደለም፤ በዚህ ረገድ፡ እግዚአብሔር፡ እስካኹን፡ ለአገልግሎት አቋማችን፡ ያደረገውን፡ የተለመደ፡ የቸርነቱንና የለጋሥነቱን ሥራ፡ ወደፊትም እስኪያበዛልን ድረስ፡ ለጊዜው፡ በእኛ በኩል፡ ዓቅማችን በፈቀደ፡ ለእናንተ የምናበረክተው አገልግሎት፡ በዚህ መልክ ከምናገኘውና አነስተኛ ከኾነው፡ ከዚሁ ገቢ ላይ መኾኑን ልታውቁት ያስፈልጋል።

3ኛ፡ ይህንኑ፡ በእኒሁ፡ በኢትዮጵያዊው ሓዋርያ ስም፡ ለእናንተ ልናበረክት ያሰብነውን አገልግሎት፡ ለእናንተም፥ ለእኛም፡ በተመቸ መልኩ ለማካኼድ ቀና ይኾንልን ዘንድ፡ "በቀበሌያችሁ ውስጥ የሚገኙት፡ ሰባቱም ሰበካ ጉባኤዎች፡ እያንዳንዳቸው፡ መርጠው በሚልኳቸው ተጠሪዎቻቸው አማካይነት፡ በአንድነት ተደራጅተው እንዲሠሩ ያስፈልጋል!" ብለን ያሳሰብናችሁና እናንተም የተቀበላችሁት አሳብ፡ ይኸው፡ በእናንተ በኩል፡ በተግባር ላይ ውሎ እየሠራ መኾኑን ማረጋገጥ ችለናል። ይኸውም፡-

፩. ከ....... ቤተ ክርስቲያን ሰበካ፡ አቶ ...............፥
፪. ከ....... " " " ቄስ ...............፥
፫. ከ....... " " " መሪጌታ ..........፥
፬. ከ....... " " " ቄስ ................፥
፭. ከ....... " " " አቶ ................፥
፮. ከ....... " " " አቶ ................፥
፯. ከ....... " " " መሪጌታ............፥

መመረጣቸውን የሚገልጸው መልእክታችሁ፡ በቅርቡ ስለደረሰን ነው።

በዚያ ስምምነታችን መሠረት፡ በእኛ በኩል፡ ተጠሪዎቻችን ኾነው እንዲያገለግሉ፡ ከካህናቱ ወገን፡ ቄስ .......ን፥ ከምእመናኑ ወገን ደግሞ፡ አቶ .......ን የሠየምናቸው መኾኑን እንድታውቁት ይኹን።

4ኛ፡ እንግዴህ፡ ለአገልግሎታችን አካኼድ አስፈላጊ የኾነው አሠራር፡ እንዲህ ከተመቻቸልን፡ በእግዚአብሔርና በቅድስት እናቱ መሪነትና ፈቃድ፥ በእኛም አገልጋይነትና መሚሪያነት፡ ለእናንተ የተጀመረው አገልግሎት፡ በምን መልኩ እንደቀጠለ፡ ከዚህ የሚከተለው አድራጎታችን በሚበቃ ይገልጽላችኋል፤ ይኸውም፡ የእኛ ተጠሪዎች፡ ለመረጣችኋቸው፡ ለእነዚህ፡ ለእናንተ ተጠሪዎች እንዲያስረክቡልን፡ ከዚህ መልእክት ጋር አባሪ አድርገን የላክንላችሁ፥ የአገልግሎታችን አጠቃላይ ድርሻ የኾነው፡ የ05ሺ (አሥራ አምስት ሺህ) ብር በረከት ነው።

ከዚህ የአገልግሎታችን በረከት ውስጥ፦

0ሺው (አሥር ሺሁ) ብር፡ በመካከላችሁ ተገኝተን ሣለን፡ በቃል አዋይታችሁን ለነበረውና እናንተም፥ እኛም፡ ቅድሚያውን እንደሰጠነው ላመንበት፥ በቅርቡ፡ ሠርታችሁ ከጨረሳችሁት በኋላ፡ በመብረቅ ተመትቶ የፈረሰውን፡ የ....... ቤተ ክርስቲያን ሕንፃ፡ መልሶ ለመገንባት ያሰባችሁትን ዕቅድ፡ ከግብ ለማድረስ የሚያግዛችሁ ይኾናል።

5ሺው (አምስት ሺሁ) ብር ደግሞ፡ በ....... ቤተ ክርስቲያን ጉብኝታችን ጊዜ፡ ከቤተሰባችን አባሎች መካከል፡ ጥቂቶቹ፡ በቀበሌያችሁ ውስጥ ያለውን ትምህርት ቤት የመመልከት ዕድል ገጥሟቸው ስለነበረ፡ በገሃድ ከታዩዋቸው፥ ከብዙዎቹ፡ የትምህርት ቤቱ አሳዛኝና አሳሳቢ ችግሮች ውስጥ፡ የመማሪያ ገበታዎችና የትምህርት መሚሪያዎች፡ ቀዳሚዎች ኾነው ስላገኘናቸው፡ ለእነዚህና በእናንተ በኩል፡ የትምህርት ቤቱን ኃላፊዎች፥ መምህራንና ወላጆች፥ ተማሪዎቹንም ጭምር በማማከር፡ "ይብሳሉ!" ብላችሁ ለምትገምቷቸው ችግሮች ማቃለያ የሚረዳ ይኾናል።

እንዲሁም፡ አኹን፡ በቅርቡ፡ ለሕመማቸው ምርመራና ለሕክምና፡ ወደ.......ከተማ መጥተው በተመለሱት፡ በቄስ ....... እና በአቶ ....... እጅ ከላክናቸው መጻሕፍቶቻችን ውስጥ፡ የቀረ ካለ፡ ከእያንዳንዱ መጽሐፍ፡ ኹለት ኹለት፥ ከሌለም፡ አንድ አንድ ቅጂ፡ ለዚሁ ትምህርት ቤት መጻሕፍት ቤት ተሰጥቶ፡ መምህራኑና ተማሪዎቹ፡ በክፍላቸውም ኾነ፡ እየተዋሱ በመውሰድ እንዲያነብቧቸው ይደረግ ዘንድ፡ ለቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ፡ በዚህ መልእክት እናሳስባለን።

5ኛ፡ ይህን፡ የአኹኑን አገልግሎት፡ ቀደም ብለን፡ ለዋናው የ....... ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ካበረከትነው፡ ከመጀመሪያው አገልግሎታችን፡ ኹለተኛና ተከታይ አድርገን፡ ለበረከት ያቀረብንላችሁ መኾኑን እንድታውቁት እንሻለን።

እስከዚህ ጊዜ ድረስ ስላለው አገልግሎታችን፡ ይህን ያህል ካሳወቅናችሁ፡ አኹን ደግሞ፡ ስለወደፊቱ አገልግሎታችን አካኼድ እንነጋገራለን።

አዎን! እንግዴህ፡ በዚሁ አገልግሎት እንድንቀጥልበት የምትፈቅዱ ከኾነ፡ "በእናንተ በኩል፡ ለፍሬ ታበቁት ዘንድ፡ ልትዘጋጁበት ያስፈልጋችኋል!" በማለት፡ በቃላችን ያሳወቅናችሁን፡ ያን፡ ዓቢይ ቍም ነገርና ከእርሱ ጋር የተያያዙትን ጉዳዮች፡ ከዚህ እንደሚከተለው፡ እንደገና በመድገምና በሦስት ወገን በመክፈል፡ አቅርበንላችኋል፤ ስለዚህ፡ ይህንኑ ቍም ነገርና ዘርፎቹን፡ በማስተዋል አዳምጣችሁ፡ በመልኩ ከፈጠራችሁ፡ ከእግዚአብሔር፡ በተፈጥሮ ባገኛችሁትና በሃይማኖት በተቀበላችሁት፡ የመምረጥ ነጻነታችሁና የመወሰን ሥልጣናችሁ ተጠቅማችሁ፡ እያንዳንዳችሁ፡ በግል፥ ኹላችሁም፡ በኅብረት፡ ለጣፋጭ ፍሬነት እንድታበቁት እናሳስባችኋለን።

## ክፍል አንድ

መቸም፡ የእውነት አምላክ የኾነው መድኃኔ ዓለም፡ ኹላችንንም፡ በእውነት እንደሚወድደንና የማያቋርጥ ቸርነቱን ዘወትር እንደሚያደርግልን ታውቃላችሁ፡፡ ከዚህ የተነሣ፡ እናንተም፥ እኛም፡ በያለንበት፡ በእውነተኛው ኢትዮጵያዊነታችን፡ እየራሳችንን፡ ለእርሱ፡ እውነተኞች አድርገን በማቅረብ፡ ፈቃዱን፡ ባስቸኳይ ለመፈጸም፡ ቆርጠን መነሣት ያለብን ጊዜ፡ ዛሬ መኾኑን፡ እናንተም፡ እንደእኛ፡ በብርቱ እንደተገነዘባችሁት እናምናለን፡፡

እዚያ እመካከላችሁ ተገኝተን ሣለን፡ በበዓሉ ላይ ሳይቀር፡ በይፋ ያደረስንላችሁንና ያሰማናችሁን መልእክት ታስታውሱታላችሁ፤ ያም መልእክት፡ ፈጣሪያችንና አምላካችን፥ ጌታችንና መድኃኒታችን፥ ካህን፡ ሊቀ ካህናታችንና ንጉሥ፡ ንጉሠ ነገሥታችን በኾነው፡ በእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ፊት፥ ደግሞም፡ እመቤታችንና አገራችን፥ ሃይማኖታችንና መቅደሳችን፥ እናታችንና ንግሥታችን በኾነችው፡ በቅድስት ድንግል ማርያም ፊት፡ እያንዳንዳችን፥ ኹላችንም፡ በአምልኳችን እውነተኞች ኾነን፥ ከየኃጢኣታችንም፡ በንሥሓ ነጽተን፡ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን ልንቀበል የሚገባን መኾኑን የሚያሳስበን የመለኮት ቃል ነው፡፡

ታዲያ፡ ያን፡ ከአደራ ጋር የተላለፈላችሁንና የሰማችሁትን የመለኮት መልእክት፡ በአኹኑ ጊዜ፡ ፈጽማችሁ የተገኛችሁ፥ ወይም፡ ለመፈጸም የተዘጋጃችሁ፡ ስንቶች ናችሁ? እግዚአብሔርንና ቅድስት እናቱን፡ እጅግ የሚያሳዝናቸው፡ ታላቁ ኃጢኣት፡ አምልኮ ባዕድ መኾኑን፡ ኹላችሁም ታውቁታላችሁ፡፡ መለኮታዊው ጥበቃና ረድኤት፡ ከሰዎች፥ በተለይም፡ "እናምንብሃለን!" ከሚሉ ሕዝበ ክርስቲያን የሚለየው፥ እነርሱም፡ በመከራና በመቅሠፍት የሚሠቃዩት፡ ከሌላው ኹሉ ኃጢኣት ይልቅ፡ እጅግ በባሰው፡ በዚሁ፡ በአምልኮ ባዕድ ምክንያት መኾኑ የተረጋገጠ ነው፡፡ ዛሬም፡ እንደቀድሞዎቹ ዘመናት፡ በኢትዮጵያውያን ላይ ደርሶ የሚታየው፡ የመከራና የመቅሠፍት ኹኔታ፡ ከዚሁ፡ ከአምልኮ ባዕድ የተነሣ መኾኑ፡ የሚጠረጠር አይደለም፡፡

ስለዚህ፡ ፈጣሪያችን፡ በቅድስት እናቱ የቃል ኪዳን አማላጅነት፡ እናንተንም፥ እኛንም፡ ይቅር ብሎ፡ ምሕረቱን እንዲያወርድልን፥ ለአገራችንና ለዓለሙም ኹሉ፡ ሰላሙን እንዲሰጥልን፡ ዲያብሎስ፡ በሰዎች ላይ አድሮ፡ በልዩ ልዩ መልክ የሚያስፈጽመው፡ ይህ፡ የአምልኮ ባዕድ ልማድ፡ ምናልባት፡ በእያንዳንዳችሁ ዘንድ፥ በየግል ሰውነታችሁ እና/ወይም፡ በየቤተሰባችሁ ውስጥ፡ በኅብረተሰባችሁም መካከል እንዳለ፡ "እባካችሁ፥ ፈጽማችሁ ተዉት! አስወግዱትም!" ብለን፡ በእግዚአብሔር ስም እንለምናችኋለን፡፡

እስኪ፡ በማስተዋል ተመልከቱት! እስካኹን፡ ይህን የመሰለው፡ አምልኮ ባዕድ፡ በዚህ መልኩ፡ ምናልባት፡ በእናንተ ዘንድ ካለ፡ በመኖሩ፡ ከመጐዳት በስተቀር፡ ከቶ፡ ምን ተጠቀማችሁ? ታዲያ! ከጉዳት በቀር፡ ጥቅም የሌለው ከኾነ፥ እንዲያውም፡ በእርሱ ጠንቅ ምክንያት፡ እናንተም ኾናችሁ፡ ልጆቻችሁ፡ በኑሮአችሁና በጤንነታችሁ የምትሠቃዩ ከኾነ፡ ከዚህ ይልቅ፡ ለምን፡ በምታምኑት ፈጣሪያችንና በቅድስት እናቱ፥ በቅዱስ መስቀሉም ኃይል፡ ፈጽማችሁ አታስወግዱትም?

ከእኛ፡ ምንም ነገር ሳይፈልግና ሳይጠይቅ፡ "በእውነትና በመንፈስ ብቻ አምልኩኝ!" ያለው፡ የቃል ኪዳን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስማ፡ እኛ፡ "ፍጠረን!" ሳንለው፡ በመልኩ ፈጥሮን፡ ከሰውነት አካላችን ጀምሮ፡ ሥነ ፍጥረቱን ኹሉ፡ ለሕይወታችን ሲሳይ አድርጎ፡ ሳንጠይቀውና ሳንለምነው፡ እንዲያው፡ በነጻና በማትረፍረፍ የሰጠን መኾኑን፥ ወደፊትም፡ የሚያስፈልገንን ኹሉ፡ ሳንጠይቀውና ሳንለምነው የሚሰጠን መኾኑን፡ ከሃይማኖታችን ተምረን አውቀናል፡፡ ደግሞም፡ እግዚአብሔርን፡ እንዴት አድርገን ልናመልከው እንደሚገባን፡ ራሱ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከዚህ በሚከተለው ቃሉ አስተምሮናል፡-

“እለ በርቱዕ በአማን ሰጋድያን፡ ይሰግዱ ለአብ፡ በመንፈስ ወበጽድቅ፤ እስመ አብኒ፡ ዘከመዝ የኀሥሥ፡ እለ ይሰግዱ ሎቱ። እስመ እግዚአብሔር፡ መንፈስ ውእቱ፤ ወእለሂ ይሰግዱ ሎቱ፡ በመንፈስ ወበጽድቅ ህለዎሙ ይስግዱ ሎቱ።”

“በቀናች ሃይማኖት ኹነው፡ ፈጣሪያቸውን የሚያመልኩ፡ እውነተኞች ምእመናን፡ እግዚአብሔር አብን፡ በመንፈስና በእውነት ያመልኩታል፤ እግዚአብሔር፡ መንፈስ ስለኾነ፥ የሚያመልኩትም፡ በመንፈስና በእውነት ሊያመልኩት ስለሚገባቸው፡ እግዚአብሔር አብ፡ እርሱን የሚያመልኩት አማኞቹ፡ እንዲህ አድርገው፡ በመንፈስና በእውነት እንዲያመልኩት ይሻል።” (ዮሐ. 4፥ "3-"4።)

እንዲህ ከኾነ፥ ይልቁንም፡ “ክርስቶስ” በተባለበት፡ በእርሱ ስም፡ እኛ፡ “ክርስቲያን”፥ እንዲሁም፡ “ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር!” በተባለችው፡ በቅድስት እናቱ ስም፡ “ኢትዮጵያውያን” ከተባልን፡ ታዲያ! ይህን፡ የእርሱን ቃል ተቀብለን፡ ለምን፡ እርሱን ብቻ አናመልክም?

እንግዲህ፡ ከአጠገባችሁ ተገኝተን፡ በቃል እንደነገርናችሁ፡ እንዲህ ያለው፡ ቸርና ርኅሩኅ አምላካችን፡ እኛን፡ መሣሪያዎቹ አድርጎ፡ ለእናንተ፡ ለሥጋዊው ኾነ ለመንፈሳዊው ሕይወታችሁ፡ የሚበጃችሁን፡ የልማትና የዕድገት መልካም ዕድል ይከፍትላችሁ ዘንድ፥ ይህንኑ የተከፈተ ዕድላችሁንም፡ በአጭር ጊዜ ውስጥ፡ ለመልካም ፍሬ ያበቃላችሁ ዘንድ፡ እርሱ፡ ፈጣሪያችን፡ ከነእናቱ፡ በቅዱስ መንፈሱ፡ በመካከላችን ሊገኝ ያስፈልገናል፤ “እስመ ዘእንቤለየሰ፡ አልቦ ዘትክሉ ገቢረ፥ ወኢምንትኒ!” “ያለእኔ ምንም ምን ልታደርጉ አትችሉም!” ባለው ቃሉ መሠረት፡ ያለእርሱ፡ ምንም ልናደርግ አንችልምና። (ዮሐ. 5፥ 5፤)

እኛ ኢትዮጵያውያን፡ ከፈጣሪያችን ጋር በተጋባነው፡ በቅዱሱ ኪዳን ምክንያት፡ ጥንትም፥ ዛሬም፥ ወደፊትም፡ የምንጠብቀውና የምንከተለው፡ የኑሮና የአምልኮ ሥርዓታችን፡ ከእግዚአብሔር፡ በቃል ኪዳን የተቀበልነው እንጂ፡ ሰዎች፥ ወይም፡ ዲያብሎስ የፈለሰፉትን አይደለምና፡ በየግል፥ በቤተሰብና በኅብረተሰብ ኑሮአችንና አምልኳችን ውስጥ፡ እንከን እንዳይገኝ፡ በብርቱ ልንጠነቀቅ ያስፈልገናል፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ተቃዋሚዎቹ አይሁድ፡ ሲፈትኑት፡ ላቀረቡለት ጥያቄ፡ ተገቢውን መልስ በሰጣቸው ጊዜ፡

“አ መደልዋን! ሠናየ ተነበየ ኢሳይያስ ላዕሌክሙ፥ እንዘ ይብል፦ 'ዝ ሕዝብ፡ በከናፍሪሆሙ ያከብሩኒ፤ ወበልቦሙሰ ነዋኅ ይርኅቁ እምኔየ፤ ወከንቶ ያመልኩኒ፥ እንዘ ይሜህሩ፡ ትምህርተ ሥርዓታተ ሰብእ።'”

“እናንት ግብዞች! ኢሳይያስ፡ ስለእናንተ፡ በእውነት ትንቢት ተናገረ፤ እንዲህ ሲል፦ 'ይህ ሕዝብ፡ በከንፈሩ ያከብረኛል፤ ልቡ ግን፡ ከእኔ፡ በጣም የራቀ ነው፤ የሰውም ሥርዓት የኾነ ትምህርት እያስተማሩ፡ በከንቱ ያመልኩኛል።'” ያለው ቃል፡ በእኛ ላይ ፈጽሞ ሊጸና አይገባም። (ማቴ. 05፥ 7-9።)

ስለዚህ፡ እርሱ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከነእናቱ፡ ዛሬ፡ በእናንተም፥ በእኛም መከከል ተገኝቶ፡ ሥራችንን ይባርክልን ዘንድ፥ በተግባራችንም፡ ይመራን ዘንድ፥ የሚያስፈልገንንም ኹሉ አሟልቶ፡ ድካማችንንና ጥረታችንን፡ ለፍሬ ያበቃልን ዘንድ፡ እኛ እንዳደረግነው ኹሉ፡ እናንተም ደግሞ፡ በየበኩላችሁ፡ ልትፈጽሙት የሚገባችሁ ግዳጅ አለ፤ ይኸውም፡ እየራሳችሁን፡ ከአምልኮ ባዕድ ነጻ አድርጋችሁና ሌላውን ኃጢአታችሁን፡ በንሥሓ አንጽታችሁ፡ ሥጋውን ደሙን በመቀበል፡ እውነተኛ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችሁንና የተዋሕዶ ሃይማኖት ክርስቲያንነታችሁን፡ ለየራሳችሁ ብቻ ሳይኾን፡ በእግዚአብሔርና በሰውም ፊት፡ በይፋ አረጋግጣችሁ መመስከር ነው። በአጠቃላይ፡ በዚህ መልክ፡ ከፈጣሪያችንና ከአምላካችን፡ ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅ አለብን። ይህን ካላደረግን፡ በየግላችንና በአገራችን፥ በዓለሙም ደረጃ የሚካኼደው መከራና መቅሠፍት፡ በበለጠ እየባሰና እየተጠናከረ ይኼዳል።

<u>ክፍል ኹለት</u>

“በእግዚአብሔር አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ ስም” የተጠመቅን ኢትዮጵያውያን፥ ወንዶችም፥ ሴቶችም፡ ኹላችንም፡ የእግዚአብሔር ልጆችና የመንግሥቱ ወራሾች፥ የሥርዓቱም አገልጋዮች መኾናችንን ልታውቁ ያስፈልጋችኋል፡፡ ከዚህ የተነሣ፡ በአምልኮ ባዕድና በሌላውም ኃጢኣት ካላረከስነውና ካላሳደፍነው፥ ይህንኑም፡ በንሥሓ ሳናጸዳውና በሥጋ ወደሙ ሳንቀድሰው ካልቆየን በቀር፡ ሰውነታችን፡ የእግዚአብሔር ጽላትና ታቦት፥ መንበርና መቅደስ እንደኾነም፡ ልታውቁት ይገባችኋል፡፡ ምናልባት፡ ይህን ምሥጢር፡ እስካኹን አልደረሳችሁበት እንደኾነ፡ “በጌታችንና በመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት፡ እያንዳንዳችሁ፡ በጥምቀታችሁ ምክንያት፡ በተቀዳጃችሁት የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ፡ ለዚህ መንፈሳዊ ክብር የበቃችሁ መኾናችሁን፡ እንግዴህ ወዲህ ተገንዝባችሁት፡ የመልካሟ የእግዚአብሔር ሕይወት ባለቤቶች ኹኑ!” እንላችኋለን፡፡

ይህን እውነታ፡ የእግዚአብሔር ቃል የኾነው፡ ራሱ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ቀድሞ፡ በዘመነ ብሉይ፡ በነቢያቱ፥ ኋላም፡ በዘመነ ሓዲስ፡ በተዋሓደው ሰውነቱና በሓዋርያቱ አንደበት በተናገራቸው፡ ቅዱሳት ቃላቱ አረጋግጦልናል፤ ከእነዚህም መካከል፡ እንዲህ የሚሉትን፡ ጥቂቶቹን እንጠቅስላችኋለን፡-

፩. ከነቢያት አንዱ፡ ኤርምያስ፡ በትንቢቱ፡ እንዲህ ይላል፡-

“"ናሁ ይመጽእ መዋዕል!" ይቤ እግዚአብሔር፤ "ወእሠርዕ ለቤተ እሥራኤል፥ ወለቤተ ይሁዳ፡ ሕገ ሐዲሰ፡፡ ወአኮ፡ ከመ ዝንቱ ሕግ፡ ዘሠራዕኩ ለአበዊሆሙ፡ አመ አውጻእክዎሙ እምድረ ግብፅ፤ እስመ እሙንቱኒ፡ ኢነበሩ በሥርዓትየ፤ ወአነኒ፡ ተሀየይክዎሙ፤" ይቤ እግዚአብሔር፡፡ "እስመ ዛቲ ይእቲ ሥርዓት፡ እንተ እሠርዕ ለቤተ እሥራኤል፡ እምድኅረ እማንቱ መዋዕል፤" ይቤ እግዚአብሔር፤ "እወዲ ሕግየ ውስተ ሕሊናሆሙ፤ ወእጽሕፎ ውስተ ልቦሙ፤ ወእከውኖሙ አምላኮሙ፤ ወእሙንቱኒ፡ ይከውኑኒ ሕዝብየ፡፡ ወኢይምህር እንከ እኁ እኅዋሁ፡ እንዘ ይብል፡ 'አእምርዎ ለእግዚአብሔር!' እስመ ኵሎሙ የአምሩኒ፡ ንኡሶሙ፥ ወዐቢዮሙ፤ ከመ እሣህሎሙ፥ ወእሥረይ ሎሙ ኃጢኣቶሙ፥ ወኢይዜከር ሎሙ አበሳሆሙ፡፡"”

“"እነሆ፥ ከእስራኤል ቤትና ከይሁዳ ቤት ጋር አዲስ ቃል ኪዳን የምገባበት ወራት ይመጣል!" ይላል እግዚአብሔር፤ "ከግብፅ አገር አወጣቸው ዘንድ፡ እጃቸውን በያዝኩበት ቀን፡ ከአባቶቻቸው ጋር እንደገባሁት ያለ ቃል ኪዳን አይደለም! እነርሱ በኪዳኔ አልጸኑምና፥ እኔም ቸል አልኋቸው!" ይላል እግዚአብሔር፡፡ "ከእነዚያ ወራት በኋላ፡ ከእስራኤል ቤት ጋር የምገባው ቃል ኪዳን ይህ ነውና!" ይላል እግዚአብሔር፡፡ "ሕጌን በልቡናቸው አኖራለሁ! በልባቸውም እጽፈዋለሁ፤ እኔም አምላክ እኾናቸዋለሁ፤ እነርሱም ሕዝብ ይኾኑኛል፡፡ እያንዳንዱ ሰው ባልንጀራውን፥ እያንዳንዱም ወንድሙን፡ 'እግዚአብሔርን እወቅ!'፡ ብሎ አያስተምርም፤ ከታናሹ ጀምሮ እስከታላቁ ድረስ፡ ኹሉ ያውቁኛልና!" ይላል እግዚአብሔር፡፡ "በደላቸውን እምራቸዋለሁና! ኃጢአታቸውንም፡ ከእንግዴህ ወዲህ አላስብምና!"” (ኤር. #1፥ #1-#4፡፡ ዕብ. 8፥ 8-02፡፡)

ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ፡ እስከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስና ቅድስት ድንግል ማርያም ድረስ ያሉትን፡ ሰባቱን ቅዱሳት ኪዳናት የያዘውን፡ ቅዱሱን ኪዳን ጠብቀን በመኖራችን፡ እውነተኞቹ የእሥራኤልና የይሁዳ ቤቶች፡ እኛ ኢትዮጵያውያን ስለኾንን፡ ይህ ቃል የተነገረው፡ ለእናንተና ለእኛ መኾኑን፥ የጸናውም፡ በእናንተና በእኛ ዘንድ መኾኑን ልታውቁት ይገባችኋል፡፡

፪. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ለደቀ መዛሙርቱ፡ “አንትሙሰኬ፡ መነ ትብሉኒ ከዊነ?” “እናንተስ፡ እኔን፡ ማን እንደኾንሁ ትላላችሁ?” ብሎ በጠየቃቸው ጊዜ፡ ቅዱስ ጴጥሮስ፡ “አንተ ውእቱ ክርስቶስ፡ ወልደ እግዚአብሔር ሕያው!” “አንተ፡ ክርስቶስ፡ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ!” በማለቱ፡ ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተነገረለትን ቃል፡ ታስታውሱታላችሁ፡፡

ያም ቃል፡- “ወአንሰ እብለከ፤ ከመ አንተ ኰኵሕ፤ ወዲበ ዛቲ ኰኵሕ፡ አሐንጻ ለቤተ ክርስቲያንየ፤ ወአናቅጸ ሲኦል ኢይኄይልዋ፡፡ ወእሁበከ መራኁተ መንግሥተ ሰማያት፤ ወዘአሠርከ በምድር፡ ይከውን እሡረ በሰማያት፤ ወዘፈታሕከ በምድር፡ ይከውን ፍቱሐ በሰማያት፡፡”

“እኔ እልሃለሁ፡- 'አንተ ዓለት ነህ፤ በዚችም ዓለት ላይ፡ ቤተ ክርስቲያኔን አንጻለሁ፤ የሲኦል ደጆችም አይችሏትም፡፡ የመንግሥተ ሰማያትንም መክፈቻዎች እሰጥሃለሁ፤ በምድር የምታሥረው፡ በሰማያት የታሠረ ይኾናል፤ በምድር የምትፈታውም፡ በሰማያት የተፈታ ይኾናል፡፡” (ማቴ. 06÷ 05-09፡፡)

ይህ ቃል፡ “እርሱ፡ ጌታችን ኢየሱስ፡ በእውነት፡ ክርስቶስ፡ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነው!” ብለው ለሚያምኑ፡ በዚያች ሰዓት፡ ከቅዱስ ጴጥሮስ ጋርና በእርሱ ጊዜ÷ ከእርሱም በኋላ ለነበሩት÷ እስከዛሬ ድረስ ላሉትና ወደፊት፡ እስከ ዓለም ፍጻሜ ለሚኖሩት ኹሉ፡ ጸንቶ ይኖራል፡፡

ይልቁንም፡ በእኛ፡ በኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ የበለጠ የጸና ኾኖ ቀጥሏል፤ ይኸውም፡ ይህንኑ፡ የቅዱስ ጴጥሮስን ቃል ተናግሮ፡ ጥምቀትን፡ ወዲያው በመቀበሉ፡ “ብፁዓንሰ፡ እለ እንዘ ኢይሬእዩኒ የአምኑኒ!” “ብፁዓንስ፡ ሳያዩ የሚያምኑብኝ ናቸው!” ለሚለው፡ ለጌታ ሉዓላዊ ቃል በቅቶ ብፅዕናን ካስገኘልን፡ ከዚያ፡ “አቤሜሌክ” ከተባለው፡ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ አንሥቶ እየተፈጸመ የሚታየው ሃይማኖታዊ ትንግርት ነው፡፡ (ዮሐ. "÷ "9፡፡)

፫. አኹን ደግሞ፡ ቀዳሜ ሰማዕት ቅዱስ እስጢፋኖስ፡ ተወግሮ የተገደለበትን ምክንያት የሚገልጸውንና በሰማዕትነት ከማረፉ በፊት የተናገረውን፡ እንዲህ የሚለውን ቃሉን እናሰማችሁ፡-

“ወአኮሰ፡ <u>ዘየኃድር ልዑል ውስተ ግብረ እደ ሰብእ፤</u> እስመ ከመዝ ይቤ ነቢይ፡- '''ሰማይኒ፡ መንበርየ፤ ወምድርኒ፡ መከየደ እገርየ፤ አየኑ ቤተ፡ ተሓንጹ ሊተ፤' ይቤ እግዚአብሔር፤ 'ወአይኑ መካን ውእቱ መካነ ምዕራፍየ፤ አኮኑ እደውየ ገብራ ዘኵሎ፡፡'''”

“ነቢዩ፡- '''ሰማይ፡ ዙፋኔ ነው፤ ምድርም፡ የእግሬ መረገጫ ናት፤ ለእኔ፡ ምን ዓይነት ቤትን ትሠራላችሁ?' ይላል እግዚአብሔር፤ 'ወይስ፡ የማርፍበት ሥፍራ ምንድር ነው? ይህንስ ኹሉ፡ እጄ የሠራችው አይደለምን?''' እንዳለ፡ ልዑል እግዚአብሔር፡ <u>የሰው እጅ በሠራችው አይኖርም፡፡</u>” (የሐዋ. 7÷ $7-%፡፡)

ቅዱስ እስጢፋኖስ፡ በሰማዕትነት ባረፈባት ዕለት፡ ያስሰማው፡ ይህ ቆራጥ ንግግር፡ ኢትዮጵያዊዉን ሰውነት፡ ለቤተ ክርስቲያንነት ያበቃውን፡ ያን፡ የኢየሱስ ክርስቶስን ሕያው ቃል፡ የበለጠ ገሃድና እውን ያደርገዋል፡፡

፬. ስመ ጥሩው ሐዋርያ፡ ቅዱስ ጳውሎስ፡ በመንፈስ ቅዱስ ተመልቶ፡ በጻፋቸው መልእክቶች ውስጥ፡ ይህን እውነታ በሚመለከት ካመለከታቸው ቍም ነገሮች መካከል፡ የሚከተሉትን ጥቅሶች፡ ለዓይነት አቅርበናቸዋል፡-

ሀ. “ኢተአምሩኑ፡ ከመ ታቦቱ ለእግዚአብሔር አንትሙ፤ ወመንፈሰ እግዚአብሔር ሳዕሌክሙ፡፡ ወዘሰ አማሰነ ቤተ እግዚአብሔር፡ ሎቱኒ፡ ያማስኖ እግዚአብሔር፤ ወቤቱሰ ለእግዚአብሔር አንትሙ ውእቱ፤ ወቅዱሳን አንትሙ፤ ወኢታርኵሱ ቤቶ ለእግዚአብሔር፡፡”

“የእግዚአብሔር ታቦቱ÷ ቤተ መቅደሱ እንደኾናችሁ÷ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንዲኖርባችሁ አታውቁምን? ማንም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ቢያፈርስ፡ እግዚአብሔር፡ እርሱን ያፈርሰዋል፡፡ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ፡ ቅዱስ ነውና፤ ያውም፡ እናንተ ናችሁ፡፡ (1ኛ ቆሮ. 3÷ 06-07፡፡)

ለ. "ኢተአምሩኑ፡ ከመ ማኅደሩ ለመንፈስ ቅዱስ አንትሙ፥ ዘኀዱር ላዕሌክሙ፥ ዘነሣዕክሙ እምኀበ እግዚአብሔር።"

"ሰውነታችሁ፡ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት፡ በእናንተ የሚኖረው፡ የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደኾነ አታውቁምን? (1ኛ ቆሮ. 6፥ 09።)

ሐ. "ወለነሰ መጽሐፍነ አንትሙ፤ ይእቲ፥ ወጽሕፍት ውስተ ልብነ፤ ወትትዐወቅ፤ ወያነብባ ኵሉ ሰብእ። ወያአምሩክሙ ከመ መልእክተ ክርስቶስ አንትሙ፡ እንተ ተልእክናሃ ንሕነ፤ ወጽሕፍት ይእቲ፥ ወአኮ፡ በማየ ሕመት፥ ዘእንበለ በመንፈስ እግዚአብሔር ሕያው፤ ወኢኮነ ጽሌ ዘእብን፡ ዘእንበለ ጽሌ ልብ ዘሥጋ። ...እስመ እምኀበ እግዚአብሔር ኃይልነ፥ ዘረሰየነ ላእካነ ለሐዲስ ሕግ፥ ወአኮ በሕገ መጽሐፍ፤ አላ በሕገ መንፈስ፤ እስመ መጽሐፍ ይቀትል፤ ወመንፈስ ያሐዩ።"

"ሰዎች ኹሉ የሚያውቁትና የሚያነብቡት፡ በልባችን የተጻፈ መጽሐፋችን፡ እናንተ ናችሁ። እናንተም፡ በሕያው እግዚአብሔር መንፈስ እንጂ፡ በቀለም የተጻፋችሁ አይደለም፤ ሥጋ በኾነ፡ በልብ ጽላት እንጂ፡ በድንጋይ ጽላት ላይ ያልተጻፈ፡ በእኛም የተገለገለ የክርስቶስ መልእክት እንደኾናችሁ፡ የተገለጠ ነው።... ፊደል ይገድላል፥ መንፈስ ግን፡ ሕይወትን ይሰጣልና፡ በመንፈስ እንጂ፡ በፊደል ለማይኾን፡ ለአዲስ ኪዳን አገልጋዮች እንኾን ዘንድ ያበቃን እግዚአብሔር፡ ኃይላችን ነው። (2ኛ ቆሮ. 3፥ 2-3።)

መ. "ወኢትኵኑ ኑፉቃነ! ወኢትሑሩ ውስተ አርዑተ፡ እለ ኢየአምኑ! መኑ ዘያስተዔርያ ለጽድቅ፡ ምስለ ኃጢአት? ወመኑ ዘይዴምሮ ለብርሃን ምስለ ጽልመት? ወመኑ ዘየኀብሮ ለክርስቶስ ምስለ ቤልሆር? ወመኑ ዘይከፍሎሙ ለመሃይምናን ምስለ ኑፉቃን? ወመኑ ዘይዴምር ታቦተ እግዚአብሔር ውስተ ቤተ ጣዖት? አኮኑ ንሕነ፡ ውእቱ ቤቱ ለእግዚአብሔር ሕያው፡ በከመ ይቤ እግዚአብሔር፦ "አነ አኀድር ኀቤሆሙ፤ ወአንሶሱ ማእከሎሙ፤ ወእከውኖሙ አምላኮሙ፤ ወእሙንቱኒ፡ ይከውኑኒ ሕዝብየ። ወበእንተ ዝንቱ፡ 'ፃኡ እማእከሎሙ! ወተፈለጡ!' ይቤ እግዚአብሔር፤ 'ወኢትቅረቡ ኀበ ርኩሳን! ወአነ እትዌከፈክሙ! ወእከውነክሙ አባክሙ! ወአንትሙኒ ትከውኑኒ ደቂቅየ፥ ወአዋልድየ!'" ይቤ እግዚአብሔር ዘኵሎ ይመልክ።"

"ተጠራጣሪዎች አትኹኑ! ከማያምኑ ጋር በማይመች አካኼድ አትጠመዱ! ጽድቅ፡ ከኃጢአት (እውነት፡ ከሐሰት) ጋር፡ ምን መሳተፍ አለው? ብርሃን፡ ከጨለማ ጋር ምን ኅብረት አለው? ክርስቶስስ፡ ቤልሆር ከተባለው የአጋንንት አምልኮ ጋር ምን መስማማት አለው? ወይስ፡ የሚያምኑ፡ ከማያምኑ ጋር ምን ክፍል አላቸው? ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስም፡ ከጣዖት ቤት ጋር ምን መጋጠም አለው? እኛ፡ የሕያው እግዚአብሔር ማደሪያዎቹ አይደለንምን? እንዲሁም፡ እግዚአብሔር፡ እንዲህ ሲል ተናገረ፦ "በእነርሱ አድሬባቸው እኖራለሁ፤ በመካከላቸውም እመላለሳለሁ፤ አምላካቸውም እኾናለሁ፤ እነርሱም፡ ሕዝቤ ይኾናሉ።" ስለዚህም፡ እግዚአብሔር፡ "ከመካከላቸው ውጡና፡ የተለያችሁ ኹኑ! ርኵስንም አትንኩ!" ይላል። ደግሞ፡ ኹሉን የሚገዛ እግዚአብሔር፡ እንዲህ ይላል፦ "እኔም እቀበላችኋለሁ፤ ለእናንተም አባት እኾናችኋለሁ፤ እናንተም፡ ለእኔ፡ ወንዶች ልጆችና ሴቶች ልጆች ትኾኑኛላችሁ።"" (2ኛ ቆሮ. 6፥ 04-08።)

ከዚህ በላይ የተመለከቱት የቅዱሳት መጻሕፍት ጥቅሶች፡ አረጋግጠው የሚመሰክሩልን፡ ጥንቱኑ፡ በመልኩ የፈጠረን እግዚአብሔር፡ እያንዳንዳችን፡ እንድንኾንለት የሚፈልገው፥ ደግሞ፡ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነትና በቅድስት እናቱ ድንግል ማርያም አርአያነት፡ እንድንኾን ያበቃንም፡ የእርሱ ጽላቶችና ታቦቶች፥ መንበሮችና ቤተ መቅደሶች መኾንን ነው።

እንግዴህ፡ “ቤተ ክርስቲያን” ብለን የምንሠራው ሕንፃ፡ ሃይማኖታቸውን፡ እንዲህ፡ በእውነተኛው የመንፈስ ቅዱስ አምልኮ አጽንተው፥ ኃጢኣታቸውን፡ በንስሓ አስወግደውና ኹለንተናቸውን፡ በሥጋ ወደሙ ቀድሰው የተገኙ ካህናትና ምእመናን፥ ወንዶችም፥ ሴቶችም፥ ሕፃናትም፥ አዛውንትም፡ በአንድነት ተሰብስበው፡ የፈጣሪያቸውንና የቅድስት እናቱን፡ የጸጋና የበረከት ማዕድ የሚሳተፉባት ናት፡፡ ስለቤተ ክርስቲያን፡ የእኛ ኢትዮጵያውያን ጸሎተ ሃይማኖት የሚለውን ቃል ስሙት፡-

“ወነአምን፡ በአሓቲ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን፡ እንተ ይእቲ፡ ዘመሠረታ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ እምጥንት፥ በኪዳነ ልቦና ዘአበው ቀደምት፥ ወዘአጽንዓት በቃለ ነቢያት፥ ወዘፈጸማ በላዕለ ኵሉ ጉባዔ ዘሐዋርያት፡፡ በውስቴታ ያቄርቡ ካህናት፡ መሥዋዕተ ሥጋሁ ቅዱሰ፥ ወደሞ ክቡረ ለኢየሱስ ክርስቶስ፤ ወባቲ ይትዌከፉ ምእመናን፡ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ዘዘዚአሁ፡፡”

“ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በአበው ልቦና በመሠረታት፥ በነቢያት ቃል ባጸናትና በሐዋርያት ጉባዔ በፈጸማት፥ ካህናት፡ የእርሱን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም፡ ለመሥዋዕትነት በሚያቀርቡባትና ምእመናን፡ ያን መሥዋዕት፥ የመንፈስ ቅዱስንም ልዩ ልዩ ጸጋዎች በሚቀበሉባት፡ በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እናምናለን፡፡” (ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት -፩ኛ መጽሓፍ፥ ገጽ ፻፹፯፤ ፪ኛ መጽሓፍ፥ ገጽ ፴፪፤ ፫ኛ መጽሓፍ፥ ገጽ ፵፡፡)

እንዲህ ከኾነ፡ ከዚህ በፊት የሠራናቸውና ወደፊት የምንሠራቸው የቤተ ክርስቲያን ሕንፃዎች፡ ከላይ፡ ተደጋግሞና በሰፊው ተብራርቶ እንደተገለጸው፡ እኛ፡ እያንዳንዳችን፡ ከየኃጢኣታችን፡ በንስሓ ጸድተንና ሥጋውን ደሙን ተቀብለን፡ እየራሳችንን፡ ለእግዚአብሔር ጽላትነትና ታቦትነት፥ መንበርነትና ቤተ መቅደስነት ካበቃን በኋላ፡ ፈጣሪያችንን፡ ከነእናቱ ለማመስገንና ሌሎቹን የመንፈስ ቅዱስ ጸጋዎች ለመቀበል፡ የምንሰባሰብባቸው ካልኾኑ በቀር፡ ከቶ ምን ይጠቅሙናል?

ይህን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ፈጽመን ካልተገኘንማ፡ “'ቅንአተ ቤትከ በልዐኒ!' 'የቤትህ ቅናት ይበላኛል!' ተብሎ እንደተጻፈ፡ 'ኢትረስዩ ቤተ አቡየ፡ ቤተ ምሥያጥ!' 'የአባቴን ቤት፡ የንግድ ቤት አታድርጉት!'” ... ደግሞም፡ “ንሥትዎ ለዝንቱ ቤተ መቅደስ! ወበሠሉስ ዕለት፡ አነሥኦ!” “ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት! እኔ፡ በሦስተኛው ቀን አነሣዋለሁ!” ብሎ የተናገረውን፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን፥ እናቱን፡ ቅድስት ድንግል ማርያምንም፡ የቱን ያህል እንዳሳዘንናቸው መገመት፡ ለእያንዳንዳችን የሚያዳግተን አይደለም፡፡ (ዮሐ. ፪፥ ፲፫-፲፯፡፡)

## ክፍል ሦስት

በአንድ ወገን፡ የቤተ ክርስቲያን ሕንጻን ስለመሥራት፥ በሌላው ወገን ደግሞ፡ እየራሳችን፡ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ስለመኾናችንና እየራሳችንን፡ ለዚህ ክብር ለማብቃት ስለመቻላችን፡ ይህን ያህል ተነጋገርን፡፡

አኹን ደግሞ፡ “እግዚአብሔር፡ ከእኛ የሚጠብቀው የሃይማኖትና የምግባር ፍሬ፡ ይህ ብቻ ሳይኾን፡ ከእነዚህ ጋር የተያያዘ ሌላ ተመሳሳይ ቍም ነገር ስላለ፡ በዚያ ላይ እንድንነጋገር ግድ ይኾናል፤ እርሱም፡ “እግዚአብሔርን፡ በበለጠ ደስ የሚያሰኘውና መልካም መዓዛ እንዳለው መሥዋዕት አድርጎ የሚቀበለው የትኛውን ነው?” ለሚል፡ የምርጫ ጥያቄ፡ የምንሰጠው ትክክለኛ መልስ ይኾናል፤ ጥያቄውም፡- “ለእርሱ የሚኾን ሕንጻ ቤተ ክርስቲያንን ብቻ፡ በየቦታው ብንሠራለት ነውን?” ወይስ፡ “በችግር እየተሠቃያችሁ የምትኖሩ፥ በመልኩ የፈጠራችሁና በቤዛነት ሙቶ ያዳናችሁ፡ እናንተ፡ እያንዳንዳችሁ፡ እየራሳችሁን ችላችሁና በየሙያችሁ ሠርታችሁ በምታገኙት ምርትና ገቢ፡ እየራሳችሁንና ቤተሰባችሁን፡ በምግብና በልብስ፥ በጤንነትና በልማት አሟልታችሁ፥ የየራሳችሁንም ቤት ሠርታችሁ ለመኖር የምትችሉበትን እውቀትና ዓቅም ብታገኙለት ነው?” የሚል ነው፡፡

እስኪ፥ በእውነት ንገሩን! "ፈጣሪያችንንና አምላካችንን፡ በበለጠ የሚያደስተው የትኛው ነው?" ብላችሁ ታምናላችሁ? አዎን! ኹሉን ለፈጠረውና ኹሉ የእርሱ ለኾነው፡ ለእርሱ፡ ለኹሉ ጌታ፡ እኛ ከምናደርግለት ይልቅ፡ ምንም ለሌለውና ጥሮ ግሮ ለሚያድረው፡ ለደካማው ፍጡሩ ቢደረግለት እንደሚፈቅድና እንደሚወድ፡ ጥርጥር የለውም፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም፡ ይህንኑ በማረጋገጥ፡ እንዲህ ሲል፡ በቃሉ ነግሮናል፡-

**"አማን እብለክሙ፤ ኵሎ ዘገበርክሙ ለአሐዱ እምእሉ ንኡሳን አኀውየ፡ እለ የአምኑ ብየ፡ ሊተ ገበርክሙ:: ...ዘኢገበርክሙ ለአሐዱ እምእሉ ንኡሳን አኀውየ፡ ሊተ ኢገበርክሙ::**

**"እውነት እላችኋለሁ፤ ከኹሉ ከሚያንሱ፡ በእኔ ከሚያምኑት፡ ከእነዚህ ወንድሞቼ፡ ለአንዱ እንኳ ስላደረጋችሁት፡ ለእኔ አደረጋችሁት:: ...ከኹሉ ከሚያንሱ፡ ከእነዚህ ወንድሞቼ፡ ለአንዱ እንኳ ስላላደረጋችሁት፡ ለእኔ አላደረጋችሁትም::**

**ደግሞም፡ "ዑቁ! ኢታስተሓቅርዎ ለአሓዱ እምእሉ ንኡሳን፤ እብለክሙ፥ ከመ መላእክቲሆሙ በሰማያት፡ ወትረ ይሬእዩ ገጸ ለአቡየ ዘበሰማያት::"**

**"ከእነዚህ፡ ከታናናሾቹ፡ አንዱን እንዳትንቁ ተጠንቀቁ! 'መላእክቶቻቸው፡ በሰማያት ያለውን የአባቴን ፊት፡ ዘወትር፡ በሰማያት ያያሉ!' እላችኋለሁና::"** (ማቴ. ፲፰፥ ፲፤ ፳፭፥ ፴፬-፵፭::)

ከላይ የጠቀስናቸው የእግዚአብሔር ቃላት ኹሉ፡ ይህን ምርጫ እንደሚያጸድቁት በግልጽ ትመለከቱታላችሁ፤ እኛም፡ የምናምንበትና አምነን፡ በተግባር ላይ ልናውለው የምንሻው፡ ይኸኛውን፥ እግዚአብሔር የሚወድደውን ምርጫ ተከትለን አገልግሎታችንን፡ ለሰዎች፥ ያውም፡ ለእናንተ ማበርከትን ነው:: ስለዚህ፡ የቤተ ክርስቲያንን ሕንጻ ሥራ በሚመለከት፡ ከላይ በተሰጠው ሓተታ መሠረት፡ እየራሳችንን፡ ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስነት ከማብቃቱ ግዳጅ ጋር አያይዘን የምንቀጥልበት ኾኖ፡ ነገር ግን፡ በይበልጥ፡ የእናንተን፡ ነፍሳዊ፥ ሥጋዊና መንፈሳዊ የኑሮ ኹኔታ ለማሻሻል፥ ለማልማትና ለማሳደግ ወደሚደረገው ጥረት ማተኮር እንዳለብን፡ ኹላችንም፡ በብርቱ ልንገነዘበው ይገባል::

እስካኹን ላነሣናቸው ቊም ነገሮች፡ ማስረጃ እንዲኾኑ፡ ከላይ፡ በየአንቀጹ ከተጠቀሱት፡ የቅዱሳት መጻሕፍት ቃላት ሌላ፡ የቀረውን ማብራሪያና ሓተታ፡ በመካከላችሁ ከታደሉትና ከተላኩላችሁ መጻሕፍቴ፡ በዝርዝር ልታገኟቸው የምትችሉ ስለኾነ፡ እነዚያን መጻሕፍት እንድታነብቧቸው፥ ወይም፡ እንዲነበቡላችሁ እንድታደርጉ የሚያስፈልጋችሁ መኾኑን በአክብሮት እንገልጽላችኋለን::

ክቡራንና ክቡራት፡-

እንግዴህ፡ እኛ፡ በዚህ አገልግሎት ውስጥ የምንሳተፍ አባሎች፡ ከፈጣሪያችንና ከቅድስት እናቱ፡ የተጣለብን አደራና ኣላፊነት አሳስቦንና መርቶን፡ ይህን መልእክት፡ ለእናንተ በማስተላለፍ፡ እነሆ፡ ተግባራችንና ግዳጃችን የኾነውን ተልእኳችንን ፈጽመናል:: የቀረው፡ የእናንተ ድርሻ ስለኾነ፡ እናንተ ደግሞ፡ እንዲሁ፡ የበኩላችሁ ተግባርና ግዳጅ የኾነውን፡ ከላይ የተጠራችሁበትንና እየራሳችሁን፡ ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስነት የማብቃት ተልእኳችሁን፡ በቁርጥ ውሳኔና በፍጹም ፈቃደኛነት እንድትፈጽሙ አደራ እንላችኋለን::

በዚህ ደብዳቤያችን ውስጥ ለሠፈረው መልእክታችን ያላችሁን አሳብ ገልጻችሁ፡ መልሳችሁን፡ እስከ... ወር ማብቂያ ድረስ እንድታስታውቁን እንጠብቃለን::

አምላከ ኢትዮጵያ፡ በቅድስት እናቱ የምሕረት ቃል ኪዳን፡ ለእናንተም፥ ለእኛም፥ ለአገራችንና ለዓለሙ ኹሉ፡ የሚበጀውን እንዲያደርግ እንጸልያለን::

በአገልግሎቱ ስም፡- የአገልግሎቱ ተጠሪ::